“ያፈቅረኛል ...... ይመታኛል ...........
የተለያዩ ስጦታዎች ያበረክትልኛል
.........ማንንም ሰው እንደኔ አፍቅሮ እን
ደማያውቅ ይናገራል”

“አንዳንድ ጊዜ እናቴን እስክትመታኝ
ድረስ አበሳጫታለሁ”

“በገዛ እጅሽ ነው ያመጣሽው
ይለኛል”

“በጣም ስላረጀሁ እራሴን መከላከል
አልችልም”

**የቤት ውስጥ በደል የደረሰባቸው ጓደኛ ካለዎት እንዳላዩ አይሁኑ።**

እንደጓደኝነትዎ መጠን አብረዋችው ይሁኑ፣ ችግራቸውንም ያዳምጡዋቸው፤

መደረግ ያለበትን ነገር ሁሉ አውቃለሁ ብለው አይገምቱ፣ በዳዩ ሰው በማያውቁበት ሁኔታ እርዳታ ይጠይቁ፤

ተበዳዩ የራሳቸውን ውሳኔ እንዲያደርጉ ይርዷቸው፤

ጓደኛዎ ለደረሰባቸው በደል ተጠያቂ እን ዳልሆኑና ሊደርስባቸውም እንደማይገባ እን ዲያውቁት ያድርጉ።

**ECDC**
901 S. Highland Street,
Arlington, VA 22204
(703) 685-0510



# በቤትዎ ሰላም የለም?

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ካውንስል አዲስ ለሚመጡ
አፍሪካውያን የቤተሰብ የሀይል
ጥቃት መከላከያና ማሳወቂያ (ማንቂያ፣ ማስጠንቀቂያ) ፕሮግራም

**Supported by funding through Family and Children’s Trust Fund (FACT)**

**የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካደረሰብዎ ሰው ጋር ተወዳጅተዋል? ወይስ አብረው እየኖሩ ነውን?**

√ ከሚመታዎ፣ ከሚገፈትርዎ፣ ከሚንቅዎና ከሚረግጥዎ፤

√ ቀናተኛ ከሆነ፣

√ ገንዘብዎን ከሚቆጣጠር፣ የት እንደሄዱን ከማን ጋር እንደሚውሉ ከሚከታተል፤ የሚሉትን ካላደረጉ ለኢሚግሬሽን ሪፖርት እንደሚያደርግብዎ ከሚያስፈራራ

**የሚከተሉት ችግሮች ያለባቸው ልጆች ያውቃሉን?**

√ የሚመገቡት በቂ ምግብ የማያገኙና ንጹህ ልብስ የሌላቸው

√ ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው በአደባባይ የሚመቷቸው፣ የሚጮሁባቸው ወይም የሚያሸማቅቁአቸው፤

**አረጋዊ በመሆንዎ** ምክንያት በልጆችዎ፣ በልጅ ልጆችዎ ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል ምቾትዎ/ጥቅምዎ እየተነካብዎች ነውን?

**ታዳጊ ወጣት ነህን/ሽን?** ተስፋ በመቁረጥ ህይወትህን/ሽን ለማጥፋት አስበህ/ አስበሽ ታውቃለህን/ቂያለሽን? መማር ዋጋ የለውም፤ መኖርስ ምን ይጠቅማል ብለሽ/ህ የምታስቢ/ብ?

**መታወቅ ያለባቸው እውነታዎች**

የቤት ውስጥ ብጥብጥ— ጥቃትን፣ ልጆችን መበደል/ቸል ማለትን፣ ወሲባዊ ጥቃትን፣ የወዳጅ የጓደኛ ሀይል ጥቃትን ፣ የአረጋዊያን መበደልን/ቸል ማለትን ያጠቃልላል።

በሴቶች ላይ ብቻ ሳይሆን ወንዶችም በደል ሊደርስባቸው ይችላል።

የበዳይነት ባህርያት ጨቋንነ ት፣ አስገዳጅነትና ተቆጣጣሪነት ናቸው

**በዚህ ረገድ ብቻዎን አይደሉም ማንም ሰው በደል ሊደርስበትና ብቻውን ሊሰቃይ አይገባም**

**የዚህ አገር ዜጋ ባይሆኑም በደል ሲደርስብዎ ወንጀል መሆኑን ይወቁ**

አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ከሆኑ 911 ደውለው ፖሊስ ይጥሩ

**ለማንኛውም መረጃና እርዳታ ለማግኘት በሚከለቱት የስልክ ቁጥሮች ይጠቀሙ**

በትዳር ጓደኛ/በፍቅረኛ ለሚደርስ በደል
(703) 838 4911

በአረጋውያን ላይ ለሚደርስ በደል
(703) 838 4911

በህጻናት ላይ ለሚደርስ በደል
(703) 527 4070

የራሰን ህይወት ስለማጥፋት
1 800 748 2433
1-800-273 8255 (National Suicide Hotline)